## ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች

(የጌታ ቀን—ሁለተኛ የማለዳ ክፍለ ጊዜ)

መልእክት ስምንት

### መለኮታዊውን ኢኮኖሚ ለማጠናቀቅ እና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለመሆን በተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የድል-ነሺ ሕይወት መኖር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- ራእ. 3፡7-8፣ 11-12፣ 21፤ 19፡7፤ 21፡2፣ 9-11

**I. ድል-ነሺዎቹ ሰባት እጥፍ ያየለ መንፈስ በሆነው በድል-ነሺው ክርስቶስ ይፈራሉ፣ እንደ የክርስቶስ ሙሽራ መዘጋጀት ለክርስቶስ አካል መገንባት ሸክም አላቸው—ኤፌ. 4፡16፤ ራእ. 5፡6፤ 19፡7-9፡-**

ሀ. ድል-ነሺዎቹ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ ለክርስቶስ አካል ግንባታ ናቸው—ኤፌ. 4፡12፣ 16፤ ራእ. 2፡7፤ 3፡12፣ 21፡-

1. ያለ ድል-ነሺዎቹ የክርስቶስ አካል መገንባት አይችልም፣ የክርስቶስ አካል እስካልተገነባ ድረስ ክርስቶስ ለሙሽራው ተመልሶ መምጣት አይችልም—19፡7-9።
2. ሰባት እጥፍ ያየለ፣ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ በሆነው በክርስቶስ የፈሩት ድል-ነሺዎች በመንግሥቱ ዘመን ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የመጀመሪያ መጠናቀቅ እና በመጨረሻ በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የመጨረሻ መጠናቀቅ በዚህ ዘመን አካሉን ይገነባሉ—1፡4፤ 2፡7፤ 4፡5፤ 5፡6፤ 3፡12፤ 21፡2።

ለ. በራእይ 2 እና 3 በእያንዳንዱ ሰባት መልእክቶች መጨረሻ ላይ ያሉት የጌታ ተስፋ ቃሎች አሁን ያለውን የድል-ነሺዎቹን ድሰታ እና በሚመጣው ሺህ ዓመት መንግሥት የሚሰጣቸውን ሽልማት ያመለክታሉ—2፡7፣ 11፣ 17፣ 26-28፤ 3፡5፣ 12፣ 21፡-

1. ወደ ጌታ ደስታ ለመግባትና በሚመጣው ዘመን ጌታን እንደ የላቀው ታላቁ ሽልማታችን ለመቀበል ዛሬ በዚህ ዘመን እርሱን ማትረፍ እና በታማኝነት እርሱን መደሰት ያስፈልገናል—ማቴ. 25፡21፣ 23፤ ፊልጵ. 3፡8-9፤ ዘፍ. 15፡1።
2. እንደ ተስፋ ቃሎቹ እውነታ ክርስቶስን በታማኝነት ካልተደሰትነው እና ካልተለማመድነው በመንግሥቱ ዘመን መፈጸማቸው ላይ አንሳተፍም፤ መርሁ እኛ የሆነው ነገር ሽልማታችን ይሆናል—1 ቆሮ. 9፡24-27።

**II. እንደ ምልክት፣ በፊልድልፍያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የተመለሰችውን ቤተ ክርስቲያንን ታመለክታለች—ራእ. 3፡7፡-**

ሀ. በፊልድልፍያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ተገቢ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሆነውን የወንድማማች መዋደድን ቤተ ክርስቲያን ትንቢታዊ በሆነ መልኩ ታሳያለች—ቁ. 7።

ለ. በፊልድልፍያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ አንድ ጎልቶ የሚታይ ነገር የጌታን ቃል መጠበቋ ነው—ቁ. 7-8።

ሐ. በራእይ 3፡8 ጌታ በፊልድልፍያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ስሙን እንዳልካደች ይናገራል፤ የጌታ ቃል መገለጡ ነው የጌታ ስም ደግሞ ጌታ ራሱ ነው—ቆላ. 3፡16-17፤ ማቴ. 18፡20።

መ. በተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው በጣም የሚያነቃቃው ምስክርነት ከሁሉም ኑፋቄዎች እና ባሕሎች ንጹህ ወደሆነው ቃል እና ሌሎችን ስሞች ሁሉ በመተው የጌታን ስም ከፍ ወደ ማድረግ መመለሷ ነው—ራእ. 3፡8።

ሠ. ለተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ጌታ ከመክፈትና ከመዝጋት ሥልጣን ጋር የዳዊት ቁልፍ፣ የመንግሥቱ ቁልፍ ያለው ነው—ቁ. 7፤ ኢሳ. 22፡22፡-

1. ይህ ለእግዚአብሔር መንግሥት መገንባት በዳዊት ቤት የተመሰለው የእግዚአብሔር ቤተ መዛግብት ቁልፍ ነው—39፡2፤ 2 ሳሙ. 7፡16።
2. የዳዊት ቁልፍ የእግዚአብሔርን ቤት ውድ መዝገቦችን ሁሉ፣ ይህም ለድሰታችን የሆኑትን የክርስቶስን ብልጥግናዎች ሁሉ ለመጠበቅ ነው—ኤፌ. 3፡8።
3. የዳዊት ቁልፍ መላው አጽናፍ-ዓለምን ለእግዚአብሔር ይከፍታል—ኢሳ. 22፡22፤ ራእ. 3፡7፡-
   - ሀ. ዳዊት የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ በመመሥረት እግዚአብሔርን የሚወክል እና የእግዚአብሔር መግዛት ቁልፍ ያለው ነው—ኢሳ. 22፡22።
   - ለ. እንደ እውነተኛው ዳዊት፣ እንደ የሚበልጠው ዳዊት፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቤት፣ እውነተኛውን መቅደስ ገንብቷል፣ እግዚአብሔርንም ለመወከል ሙሉ ሥልጣኑን የሚያንቀሳቅስበት አገዛዝ የሆነውን የእግዚአብሔርን መንግሥት መሥርቷል፤ ስለዚህ የዳዊትን ቁልፍ ይዟል—ማቴ. 1፡1፤ 12፡3-8፤ 16፡18-19።
   - ሐ. ክርስቶስ የዳዊት ቁልፍ ያለው የመሆኑ ሀቅ የሚያመለክተው እርሱ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከል እንደሆነ ነው፤ እግዚአብሔርን የሚገልጠውና የሚወክለው፣ በእግዚአብሔር አገዛዝ ሁሉንም ነገር ለመክፈት ቁልፉን የያዘው እርሱ ነው—ቆላ. 1፡15-18።

III. **ጌታ ኢየሱስ በተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ድል-ነሺ በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ የተገነባ ዓምድ ያደርገዋል—ራእ. 3፡11-12፦**

ሀ. ጌታ እኛን በመለወጥ፣ ማለትም ተፈጥሮአዊ ንጥረ-ነገራችንን በማስወገድ እና በመለኮታዊው ውስጠ-ነገሩ በመተካት ዓዕማድ ያደርገናል—ሮሜ 12፡2፤ 2 ቆሮ. 3፡18፦

1. በራእይ 3፡12 *ሊያደርገዋለሁ* የሚለው ትርጉም ወደ ሆነ ነገር እኛን ማቀናበር፣ በመፍጠር መንገድ እኛን መገባንት ነው።
2. ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጌታ ራሱን ወደ ውስጣችን እየሠራና እኛን በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ ዓዕማድ እያደረገን እና እያቀናበረን አለ።

ለ. በራእይ 21፡22 በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሦስታንዱ አምላክ ራሱ መቅደሱ እንደሚሆን እናያለን፦

1. ድል-ነሺዎቹ በመቅደሱ ውስጥ ዓዕማድ መሆናቸው ማለት በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ዓዕማድ ይሆናሉ ማለት ነው—3፡12።
2. ይህ ከሦስታንዱ አምላክ ጋር መዋሐድንና በእርሱ መቀናበርን ያካትታል—ኤፌ. 3፡16-17።

ሐ. በዛሬው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንኳን ሳይቀር ድል-ነሺ የሆኑት ቅዱሳን በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ያሉ ዓዕማድ ናቸው—ራእ. 3፡12፤ ገላ. 2፡9፦

1. እነዚህ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያንን ተምሳሌት በሆኑት በወርቃማዎቹ መቅረዞች እንደተመለከተው ቤተ ክርስቲያን በእርግጥ ከሦስታንዱ አምላክ ውጪ ሌላ ምንም ስላለመሆኗ አንዳንድ ጊዜ ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ አላቸው—ራእ. 1፡12፤ 20።
2. ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ዓዕማድ በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ያሉ ዓዕማድ ናቸው፤ በሚመጣው ዘመን እነዚህ ድል-ነሺ አማኞች በእግዚአብሔር መቅደስ፣ ማለትም በእግዚአብሔር በራሱ ውስጥ ዓዕማድ ይሆናሉ—3፡12፤ 21፡22።
3. ከዚህ የምናየው ዓዕማድ መደረግ ሦስታንዱ አምላክ ታማኝ ከሆኑ አማኞቹ ጋር መዋሐዱን እና ወደ እነርሱ ውስጥ መቀናበሩን እንደሚያካትት ነው—2 ቆሮ. 13፡14።

መ. በፊልድልፍያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ድል-መንሣት በጌታ ምለሳ የተቀበልነውን እስከመጨረሻ መጠበቅ ነው፤ ይህን ካደረግን ጌታ በእግዚአብሔር መቅደስ ዓምድ ያደርገናል—ራእ. 3፡11-12።

IV. **በተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ድል-ነሺ በሂደት ባለፈው እና በተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ የተቀናበረ ነው እንዲሁም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ "ሙሽራይቱ፣ የበጉ ሚስት" ይሆናል—ቁ. 12፤ 21፡2፤ 9-11፦**

ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስ ገዢው ራእይ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ቤተ ክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ አካል ለማፍራትና ለመገንባት መላው ማንነታቸውን በመለኮታዊው ሥላሴ ለማጥለቅለቅ ሦስታንዱ አምላክ ወደ መረጣቸውና ወደ ዋጃቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን መሥራቱ ነው—ኤፌ. 4፡4-6፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10።

ለ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መለኮትና ሰብዕና እንደ አንድ አካል የመዋሐዳቸው፣ የመጋጠማቸው እና አብሮ የመገንባታቸው የጥበብ ውጤት ናት፤ የሚያዋቅሯት ክፍሎች ሁሉ አንድ አይነት ሕይወት፣ ባህሪ እና ቅንብር አላቸው ስለዚህም ብዙዎች የተካተቱበት አንድ ማንነት ናቸው—ዮሐ. 14፡20፣ 23፤ ራእ. 21፡2-3፣ 9-23፦

1. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊ ራእይ እና የመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛው ጫፍ መጠናቀቅ ናት—ቁ. 2፣ 9-11።
2. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር የተመረጡ፣ የተዋጁ፣ ዳግም የተወለዱ፣ የተቀደሱ፣ የታደሱ፣ የተለወጡ፣ የመሰሉ እና የከበሩ መለኮት የተደረጉ ሕዝብ ጥበባዊ ውህድ ናት—ዮሐ. 3፡6፤ ዕብ. 2፡11፤ ሮሜ 12፡2፤ 8፡29-30፦
   ሀ. መለኮት መደረጋችን ማለት በሂደት ባለፈው እና በተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ እየተቀናበርን ነው ማለት ነው፣ ይህም ለዘላለም የጋራ መገለጡ ለመሆን በሕይወትና በባህሪ እግዚአብሔር እንደረግ ዘንድ ነው—ራእ. 21፡11።
   ለ. የአማኞች መለኮት መደረግ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቅ ሂደት ነው፤ ይህ ከፍተኛው እውነትና ከፍተኛው ወንጌል ነው—ሮሜ 1፡1፣ 3-4፤ 5፡10፤ ራእ. 21፡2፤ 3፡12።

ሐ. "የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፣ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፣ አዲሱንም ስሜን በእርሱ [በድል-ነሺው] ላይ እጽፈዋለሁ"—ቁ. 12፦

1. የእግዚአብሔር ስም፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስም እና የጌታ አዲስ ስም በድል-ነሺው ላይ የመጻፋቸው ሀቅ የሚያመለክተው ድል-ነሺው በእግዚአብሔር፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እና በጌታ የተያዘ እንደሆነ፤ እግዚአብሔር ራሱ፣ የእርሱ ከተማ (አዲሲቱ ኢየሩሳሌም) እና ጌታ ራሱ የእርሱ እንደሆኑ፤ እና ከእግዚአብሔር ጋር፣ ከአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ጋር እና ከጌታ ጋር አንድ እንደሆነ ነው።

2. የእግዚአብሔር ስም እግዚአብሔርን ራሱን ያመለክታል፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስም ከተማይቱን ራሷን ያመለክታል እና የጌታ ስም ጌታን ራሱን ያመለክታል—ቁ. 12።
3. የእግዚአብሔር ስም፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስም እና የጌታ ስም በድል-ነሺው ላይ መጻፋቸው የሚያመለክተው እግዚአብሔር የሆነው፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ባህሪ እና የጌታ ማንነት ሁሉ ድል-ነሺው ውስጥ መሠራቱን ነው—ዮሐ. 14፡19-20፣ 23፤ ኤፌ. 3፡16-17።
4. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለድል-ነሺው እንደ ሽልማት መጠቀሷ የሚያመለክተው ይህ ተስፋ ቃል በሺህ ዓመቱ መንግሥት እንደሚፈጸም ነው፤ በሺህ ዓመቱ መንግሥት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለድል-ነሺዎቹ ብቻ ሽልማት ትሆናለች—ራእ. 3፡12።

*© 2021 Living Stream Ministry*